እጆቼን ዘርግቼ አንተን አመልካለሁ
በፍፁምም ልቤ ምስጋና እሰዋለሁ
ተባረክ እልሀለው ተባረክ እልሀለው
ከፍ በል እልሐለው ከፍ በል እልሐለው

አንተው በፈጠርከው እህህህ በሁለመናዬ አሀሀ
አኔ አመልክሐለው አሆሆ ተመሰገን ጌታዬ /2/

እኔነት የለኝም እኔ ያንተ ሆኜ

ደምህን አፍሰህ በዋጋ የገዛህኝ

በራሴም አላዝም አዛዥ አንተ ነህ

ሁሌ በአይምሮዬ ትመራኛለህ

በፍፁም ልቤ በፍፁም ሐሳቤ

በፍፁም ነፍሴ ላምልክህ የሱሴ 2

ጌታ ክበር እልሐለዉ

የሱሰ ንገሰ እልሐለዉ

ያደረከውን እያየሁ

እንዴት እንዴት ዝም እላለሁ

ነፍሴ አንተን ታከብራለች

አምላኬ ጌታዬ ነህ እያለች

ባለ ዉለታዋ ነህና

ታቀርብልሀለች ምስጋና

ጌታ ክበር እልሃለሁ
የሱስ ንገስ እልሃለሁ
ያደረከውን እየየሁ
እንዴት እንዴት ዝም እላለሁ

በፍፁም ልቤ በፍፁም ሐሳቤ
በፍፁም ነፍሴ ላምልክህ የሱሴ

እግዚአብሄር
ረጅምና ከፍ ባለው ዙፋኑ ላይ ያለህ
<u>አንተ ብቻ የበላይ ነህ</u> (4)

የዘመንህ ቁጥር አይመረመርም
ግዛትህ ዳርቻ ፍፃሜ የለውም
አልፋና ኦሜጋ ፊተኛ ኋለኛ
አንተ እግዚአብሄር ነህ ብቻህን ገናና

ካንተ በቀር ሌላ (2) ሌላ አምላክ ማነው
ካንተ በቀር ሌላ (2) ሌላ ንጉስ ማነው
ካንተ በቀር ሌላ (2) ሌላ የበላይ ማነው
ካንተ በቀር ሌላ (2) ሌላ ገዢ ማነው

አምላክ አንተ ብቻ ገዢ አንተ ብቻ
ንጉስ አንተ ብቻ <u>ዘላለም የሌለህ አቻ (8)</u>

ከፍ ካለው በላይ ከፍ ከፍ ብለህ
በስልጣን በሞገስ ፀንተህ ትኖራለህ
ግርማዊነትህም አለምን ሞልቶታል
ፍጥረት ሁሉ ላንተ ይገዛልሃል

ካንተ በቀር ሌላ (2) ሌላ አምላክ ማነው
ካንተ በቀር ሌላ (2) ሌላ ንጉስ ማነው
ካንተ በቀር ሌላ (2) ሌላ የበላይ ማነው
ካንተ በቀር ሌላ (2) ሌላ ገዢ ማነው
እግዚአብሄር ...

ከኔ በፊ አባቶቼ ከነሱም መላእክቱ
እንዳመለኩት አይደለም ሳመልከው የቆምኩት በፊቱ
እኔ ግን በክርስቶስ የተደረገልኝ መዳኔ
የምስጋናዬን ሚዛን ደፋ ያደርገዋል
ተራው ከደረሰኝ አለኝ የማወራው
እድሉን ካገኘሁ አለኝ የማወራው
መሸ ነጋ አልልም አለኝ የማወራው
ክረምት በጋ አልመርጥም አለኝ የማወራው

ካንተ ጋር የሚቆም ደፍሮ የሚወዳደር
የበላይ አሃ አሃ የበላይ ነህ
አልተገኘም በምድር ከጫፍ ጫፍ ቢቆጠር
የበላይ አሃ አሃ የበላይ ነህ
ስምህ ብቻ አይደለም ስራህ ይናገራል
የበላይ አሃ አሃ የበላይ ነህ
የትኛው ጀግና ሰው መቃብር ፈንቅሎአል
የበላይ አሃ አሃ የበላይ ነህ

የበላይ ነህ ጌታ የበላይ የሁሉ በላይ
በላይ በላይ በላይ የበላይ በላይ በላይ

የበላይ ነህ ጌታ የበላይ በላይ
በላይ በላይ በላይ የበላይ በላይ በላይ

ብዙ ኃያላንን በምድር ላይ አይተናል
ማህደር ሲገለጥ ታሪክ አንብበናል
የትኛው ጀግና ነው ሞትን ያሸነፈው
ስንቱ ወንድ አይደል ወይ መቃብር የዋጠው

አንተ ግን ከፍ ብለሃል
ሞትና መውጊያውን ሰብረሃል
ልኩራ እንጂ በአንተ እንዴት ልፈር (2)
ጌታ ነህ ታሪክ ይናገር

እስቲ ይናገሩ ሰማይና ምድር
የበላይ አሃ አሃ የበላይ ነህ
የታሪክ አዋቂ ይጠራ ምስክር
የበላይ አሃ አሃ የበላይ ነህ
ከአንተ በላይ ጌታ ሞትን ድል ያደረገ
የበላይ አሃ አሃ የበላይ ነህ
የበላይ ነህ ጌታ የበላይ በላይ
በላይ በላይ በላይ የበላይ በላይ በላይ
እረ ማን ነው እሱ በክብር ያረገ

የበላይ ነህ ጌታ የበላይ የሁሉ በላይ
በላይ በላይ በላይ የበላይ በላይ በላይ